## ምዕራፍ ፳ ወለጋ፡ ክናድ ።

### መግለጫ።

በወርቅ ከታወቁት የኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች አንዱ ወለጋ ነው ። ክናድም የተባለው አምባር ከክንድ ላይ ስለሚውል ነው ። ዱሩ ብዙ ደኑ ሰፊ፡ ዛፉ ረጃጅም ጫካው ጭፍቅ መሆኒው ጥቅጥቅ ስለሆነ በእያንዳንዱ አውራጃ ከኢሉባቦርና ከከፋ የሚወዳደሩ ዛፎች ያበቅላል ። በዴዴሳ ባንገር፡ በበሎ በረሃ ታላላቆች አራዊት ዝሆንና አንበሳ ሳይቀር ይገኙበታል ። በወለጋ የማይበቅል እህል የለም ፤ ቡና አለ አማራ የማያውቃቸው ጐደሬ አንጮቴ፡ ቦይና ወርቄ የሚባሉ የሥራሥር ምግቦች አሉ ። ሰው በባለ እጅነት በኩል በጣም የሠለጠነ ነው ።

በግምቢ ብረት ያወጣሉ ፤ የዕንጨት መመገዣ መኪና አላቸው ።

ዓሣ ያላቸው ወንዞች ፤ ዴዴሳ፡ አንገር፡ ባሮ፡ ግቤ ናቸው ፤ ከእነዚህም ሌላ ብዙ ምንጮችና መዋቶች አሉ ።

አውራጃዎች ፡ ሀ) ነቀምቴ፡ ለ) ጉድሩ፡ ሐ) ቄለም፡ መ) አርጆ፡ ሠ) አሱሳ፡ ረ) ግምቢ ናቸው ።

ወሰን ፤ በሰሜን ጐጃም፡ በምዕራብ ሱዳን፡ በደቡብ ኢሉባቦርና ከፋ፡ በምሥራቅ ሸዋ ይዋሰኑታል ።

በየዱሩ የሚበላ ሥራሥርና ፍራፍሬ ሞልቷል ፤ የላስቲክ ሐረግ በብዙ ይገኛል ።

ልብ

ክናድሽ ወለጋ ወርቅ ያሠርሽበት
የተጥለቀለቀው በውብ ደም ግባት
ዓለሙን ሠቀየ ማረከ ፍጥረት ።
ያየሽ ተደነቀ ተገረመልሽ
አልፎ ሃጁ ሁሉ ነሆለለብሽ ።
ባሻጋሪ ሲያዩት የሚያብረቀርቅ
አሥረሽ ብትታዪው መጠን የለሽ ወርቅ
አንድ ወቄት አይደለም ወይም መሐለቅ
መጠኑን ዲካውን ማንም ሰው ሳያውቅ
ክናድሽን እያየ ይላል ዕፁብ ድንቅ ።
ከክርን እስከ መዳፍ የተሸከምሺው
እማዬ ይህን ወርቅ የት አገኘሺው ።
ከክንድሽ ላይ ያለው የጠራው ወርቅሽ
ይደርሳል ብትናኚው ለመላ አካልሽ ።
እማዬ በወርቅሽ ስትሽሞነሞኝ
እንኳንስ ባዳውን ልጅሽን ገረመኝ ።
ስትንቂው የማይሽ እንዳፈር ወርቁን

የምታገኝበት በታው የት ይሆን?

<u>ኢትዮጵያ</u>      ወርቅን ናቀች ብለህ ልጄ አይግረምህ
ተከተለኝማ ትንግርት ታያለህ
ካፈሬ ስለቅም እንደ ደንጊያ ወርቅ
ብዝቀው ብዝቀው መቸውንም አያልቅ ።
ባሱማ በቤጊ በቄለም በሾንካ
የሚዛቀው ወርቄ ወገን የሚያስመካ ።
እበላለሁ ጮማ እንደ ልብ <u>በይብዶ</u>
ጠጅም እጠጣለሁ ወርቅ ሳለ ምን ገዶ ።
ልጆቼ ወጡና በግምቢ በስቡ
ወርቅ እስቲ በቃቸው ተግተው ሰበሰቡ
ዝናም ዘንሞ ዘንሞ በክረምት ዘመን
ሲጠርገው መሬቱን ሲያጥበው ሣሩን ።
ከረጢቱን ይዞ ወርቅ የሰበሰበ
ባንድ ጊዜ ይከብራል ደኃውም ካሰበ ።
እንኳንስ ለራሴ ላለም ብናኘው
የሚፈላው ወርቄ በቄላ ደጋው
ይበቃል ለሁሉ ማለቂያም የለው ።
ደኃይቱ ስታጣ ለልጇ ወተት
ራብ ሲጠናባት ችጋር ሲይዛት
ብዙ ተባይ ያላት የልጆች እናት
ልባማ ታታሪ ጠንቃቃዋ ሴት ።
ትለቃቅምና ከጓሮ ወርቁን
ገዝታ ትመጣለች ሚያስፈልጋትን ።
ይዛ ትደርሳለች ሁሉን አንድነት
ጮማና ብርንዶ ማርና ወተት
ያገሬ ኰበሌ ተነሥቶ ማለዳ
ሥጋ ሲናፍቀው <u>ውል</u> ሲለው ሉካንዳ
ወርቅ ጋፎ ይመጣል ሂዶ ምድረ በዳ ።
በሾንካና ይብዶ በአሱማ በቤጊ
ወርቅ አብሮ ይገኛል ከቤቱ ጥራጊ ።
አውግቼና አውርቼ ለፍልፊም አያልቅ
ክናዴ ወለጋ ማድን ነው የወርቅ ።

<u>ልብ</u>      ወርቅ ብቻ ከሆነ መንደሩ ዱዱ.ው
ደኑ ሸንተረሩ ጫካው በረሃው

ጋራና ጉብታ አረህ ተራራው
አቀበት ቊልቍለት ደጋና ቈላው
እንኳንስ መሣሪያ ልብስ ብታደርጊው
አልጋ ብታሠሪው ብታነጥፊው
አፈርሽ ወርቅ ነው ልቤም ተረዳው ።
ወርቅ አፈር ከሆነ ዝቆ መሸከም
ባለጸጋ ሁሉ አይቸግረውም ።
አወጣ አወረደ ሁሉን ኩላሊቴ
ልቤ አሰለሰለ ተገረመ አቲቴ ።
ናላዬ ዞረብኝ ተደነቀ አንጎሌ
ዐይቶ ስላማያውቅ የጌጥሽን ምሳሌ ።
ጥበቡን ሥራውን ሳያሰላስል
ባለጸጋው ሁሉ በወርቅ ያጌጣል
ጌጡን ለመሥራት ግን ያላንዳች አመል
በጣም ያስፈልጋል ጥበበኛ አንጎል ።
ስለዚህ እማዬ ንገሪኝ ልረዳው
የዚህ ሁል መሣሪያሽ አንጥረኛው ማነው ።

ኢትዮጵያ    አንጥረኛው ማነው ብለህ ከጠየቅህ
መጠየቅህ ላይቀር ትንሽ ቈይተህ
ባለእጅ ደበናንሳ ሽማኔ ብለህ
ሁሉንም አንድነት አሁን ብነግርህ
ይሻል ይመስለኛል ስማ ዝም ብለህ ።

ልብ    እረ እሰይ ! እምዬ የልብ ዐውቃ ነሽ
ቀጥዬ እሰማለሁ ጣፋጭ ነው ወግሽ ።

ኢትዮጵያ    ጌጣጌጥ በመሥራት አቻ የሌለኝ
ፋቂ ደበናንሣ አንጥረኛ ነኝ ።
በግንቢ በሊሙ በቄለም ባሱሣ
ልጄን አስተምሬ ፋቂ ደበናንሣ ።
በኮምቶ ባዱሬ ደግሞውም በሚጅራ
ያሳደግሁት ልጄ አናፂው ሲሠራ
በኩርፌ ያለውም ፋቂና ሽማኔ
በሚሠራው ጥበብ ይኩራል ወገኔ
ስለዚህ እናውጋ ሁሉንም በተራ
አንድ ባንድ እያልነ የባለጁን ሥራ ።
ከሁሉ አስቀድሜ ላንሣ አጥረኛን

ወርቁን እየሠራ የሚያኰራኝን ።
ያፈስና ወርቁን በሰም በከውር
ኰልቶ ያወጣዋል ለጌጥ ለክብር ።
አለልህ ብዙ ዓይነት ይህን የሚያስረዳ
ድሪና ጉትቻ ርባንና ማርዳ
አልቦና አሸን ክታብ አድርጋው ኰረዳ
ብቅ ስትል ገበያ ይመስላል እንግዳ ።
ይማርካል አንጒል ያዞራል አውታር
አድርገውት ሲታይ የሴት ወይዛዝር ።
አንድ ጊዜ ብታየው ሲያፈሰው ወርቁን
አንጠረኛ ልጄ ሲያቀልጠው ብሩን ።
ርባኑን ሲሠራ አልቦውን ሲለቅም
ለጥበቡ ሁሉ ወደር የለውም
ብልኀተኛው ልጅሽ ሥራው ነው ለብቻ
ዓለሙን ቢዞሩ አይገኝም አቻ
ብለህ ትሄድ ነበር ሲደክም ዐይንህ
እሱ የሠራውን ማየት ሰልችቶህ ።
አሁን የት ይገኛል ይህን የሚያህል
ጥበቡና አረጉ ያንበሳው ምስል ።
ደግሞም የዚህ ወንድም አለልህ ሸማኔ
በሥራው በግብሩ ሲኰራ ወገኔ
ጠላቴ ሲዳዳ ደስ ይለኛል እኔ ።
ቅርቃኅ ከደጋ ጥጡን ከቈላው
ሰብስቤ አመጣና ምንም ሳይቀረው ።
በርትቼ አሳስቼ ጠንክሬ አመልምዬ
ስስበው አድርና ሌሊቱን ቁጭ ብዬ ።
ፈትዬ ስጨርስ ድርና ማጉን
ልጄ ይሠራዋል ጥበብ ኵታውን ።
ብልከውንና ያማረውን ሸማ
እንድትወጣ ልጄ አምራ ተሸልማ
ፈትዬ ሳለብሳት እናትህ በክንዴ
ባሻገሪ ሲያዩዋት ታምራለች ዘመዴ ።
ሰለቸህ መሰለኝ ብዙ ባወጋህ
ዐይንህ ነሁለል አለ ደከመ ልብህ ።

 ባድንቆት ተውጬ ብመስልሽም 

በዩ· አውጊኝ እማዩ እሰማለሁና
መቼም አይጠገብ እንዲህ ያለ ዜና ።
አእምሮ ይስላል ያጓጓል ልቡና ።

<u>ኢትዮጵያ</u> ይታደስ አንጐልህ ሰውነትህ ይዝና
ብዙ ስንለፈልፍ ላስፈላልህ ቡና ።
እየዛቅህ ጨምረው እንደፈቃድህ
ማሩና ቅቤውም ይኸው ከፊትህ ።

<u>ል ብ</u> እማዩ ግሩም ነው በጣም ይጣፍጣል
የትኛው መሬትሽ ይህንን ያበቅላል ።

<u>ኢትዮጵያ</u> ነቀምቴና ግምቢ አሱሣ ቄለም
የሚበቅለው ቡና ዲካ የለውም ።
በቄለም አውራጃ ጫካ ነው ቡናው
ከመሬት ላይ ቁሞ ማነው ሚለቅመው ።
ከላዩ ላይ ወጥቶ እንደ ዋርካ ሁላ
ሲለቅመው ይውላል የመንደር <u>ወይላ</u>
ተስቦ ተሰቅሎ በእያንዳንዱ ባላ ።
ሚበቅለው ቡናዩ በየወረዳው
በቁመት በግንዱ ዛፍ ነው ሚመስለው ።
መልቀም መሸምጠጡ በጣሙን ሲያይል
ከባላው ላይ ሁኖ ያራግፈዋል ።
ወደ ጥንት ወጋችን እስቲ እንመለስ
ሸማኔ አንጠረኛ ጠቢብ እናስታውስ ።
ሸማኔ አንጠረኛ አውግቼሃለሁ
ደግሞ ስለጠቢብ እቀጥላለሁ ።
በግንቢ በቄለም ብረቱን አውጥቶ
ልጇ ይሠራዋል ሁሉንም አስማምቶ ።
አፈሩን አንጥሮ አውጥቶ ብረት
ይሸጠዋል ልጇ በብዙ ጭነት ።
ብረቱን አቅልጦ አድቦለቦለና
ለወጠው በበቅሎ ሸጠው በመሲና ።
አፈሩን አናፍቶ በታላቅ ወናፍ
አነጠረ ብረት ለዓለም የሚተርፍ ።
በማናፌያ አናፍቶ አንጥሮ በከውር
ብረትና ወርቁን ይለያል ካፈር ።
ለይቶ ለይቶ ሁሉን በረገድ

ማረሻና ወገል ገለዶ ማጭድ
መጥረቢያና ምላጭ ምሣር  ለገበሬ
ሰይፍና ጐራዴ ሾተልና ጩሬ
ለሀገር ጠባቂ ጀግናው ወታደሬ ።
አሰናድቶ ሠራ ጋሻና ጦሩን
የቦና ወለጋ የሰይፍ አፎቱን ።
ካራና ቢልዋ በጣሙን ስለት
ያዘጋጃልና ለድግሴ ለት ።
ሲሠራ ባየኸው በጃቶ በኩርፌ
የዕንጨት መፈልፈያ መሳፈቻ ወስፌ ።
እረ ስንቱን ስንቱን ስንቱን ቈጥሬው
ያናጊው መሣሪያ የዕንጨት መቅረጫው ።
በቈለም ከተማ በግንቢ መንደር
የዕንጨት መፈልፈያ አለኝ መዝወር ።
መጋዝ መላጊያውን ራሱ ሠራና
በደንብ አዘጋጀው የዕንጨቱን መኪና ።
ይህንን መኪና መጋዙን ሳየው
በጣም ያኰራኛል የልጄ ሥራው ።
የብረቴ ሥራ በጣም ብዙ ነው
ሆሉን እንዳልነግርህ ያጥረናል ጊዜው ።
ብረቱና ወርቁ እስከዚህ በቅቶን
አንጣጩን ዕንየው ቀንደ ሠሬውን ።
ጥሩውን ጐሽ ዋንጫ ልዩ ልዩ ቀለም
ይሠራዋል ግንቢ ይነጠዋል ቈለም ።
እጅግ ጥሩ ዕቃዎች ከመለኪያ ጋራ
በጣም ያስደንቃል ላየው ሁል ሲሠራ ።
ዓለም የሚያስገርም የሚያስደነግጥ
ከዝሆን ጥርስ ሠራ ልዩ ልዩ ጌጥ ።
በሐረግ ያጌጠ አልጋና ዙፋን
ከዝሆን ጥርስ ሠርቶ ሰጠው ለመስፍን
የሚሠራውን ጌጥ አቅዱ የተስማማ
ስንቱን ልቍጠርልህ በግንቢ ከተማ ።
ስለአንጣጭ አወጋን ዐየን ዕቃውን
ዋንጫው የጎሽ ቀንድ ጌጡ የዝሆን ።
ለቀቅ እናርግና የጠቢቡን ተራ

ጐብኝተን እንለፍ የአናፂውን ሥራ ።
ዕየው ተመልከተው በቅጥ ሁሉንም
ሕሊና ሚማርክ ልብ የሚያስገርም ።
የዚህ ልጁ ሥራ ይገርማል በጣም
በግንቢ ነቀምቴ አሱሳ ቈለም
ዕንጨቱን ሲሠራው እንከን የለውም ።
ኮርቻና ሻንጣ ቅንባና ጥራር
ገበታና ሣጥን በሊሙ መንደር
ዘለዓለም ይሠራል አልጋና ወምበር ።
ቅርጫትና ማንካ ማበጠሪያ ሚዶ
በአሱሣ በግንቢ በሊሙ በይብዶ ።
ያበጃል ቅርቅኍ ሰዴቃና አቴና
ኰፋዳና ጥራር አገልግል ጋዘና
ሽመሉን ሰንጥቆ እንደ ዘነዘና
ሞሰብና ሌማት ዕንቅብ ታላቅ ቁና
ጠላልፎ ጠላልፎ ያወሳስብና ።
የገበሬ ምሳ ማመላለሻው
ሰሌን አኮፋዳ መስሎ ሚታየው
ሽመል ቅርቃኍ ነው ቅረብና ዕየው ።
ደንቀዝና ወምበር ጌጣቸው አማረ
ማቶት ጠረጴዛ መልካቸው ሠመረ
አርጬሜ ብርኩማ ቅርጻቸው በረረ
በመልካም መሣሪያ ከተሰረሰረ ።
ሐረጋቸው ጐላ ቅርቡድ ወምበር
ቢፈለፍላቸው በቅርጽ በመሥመር
በያዘው መኪና ባለው መዘወር ።
ስልታቸው ተስማማ ሳንቃና ጉበን
የበር ቆመ ብእሲ መድረክ ከመቃን ።
ብልሃተኛው ልጁ ጥበብኛው ወንድ
ተመልከት ሲሰጠው ለሁሉም መንገድ ።
ዕፁብ ነው ድንቅ ነው የልጁ ጥበቡ
የሚሠራው ዕቃ ነጆ መነሲቡ ።
ባየኸው ሲሠራ ገበቴ ወራንታ
በጣም የሚያስጐመጅ ቀለምሽሽ ገበታ ።
ጥበቡ የሚገርም ሥራው አስደናቂ

ያናጢ ኋደኛ አለኝ ጥሩ ፋቂ ።
ላምነትና ጀንዲ ትራስና አንቀልባ
ቆርበቱን ሲያለፋው ይመስላል አበባ ።
እንዳያ ሲለሰልስ የበና ጠፍር
ደሳሰህ ብታየው እንደምን ያምር ።
በጭር ከነገርሁህ የወንዶችን ሥራ
የሴቲቱን ደግሞ እናውጋ በተራ ።
ተስማምቶ ለሚያየው ምጣድና ሙግዱ
እጅግ ያስደንቃል ያስጐመጃል አቅዱ ።
ጅበናና ኩስኩስት ገንቦና መንቀል
አሳዳሪው ጋኗ የለውም አምሳል ።
ሳሌ ትልቅ ቧዴ ማድጋና እንሥራ
አሽፋትና ኮልባ ቶፋዋና ጣራ ።
አፍላል ከሰታቴ ድስትና ወጭት
የምትሠራው ሁሉ ይመስላል ወሊት ።
የልጆቼን ሙያ ያስተማርሁትን
በመላ እንኳ ባይሆን ኋሌ ኋሌውን
እነሆ አሳየሁህ ነገርሁህ ሁሉን
እንቀመጥና ቡና እየጠጣን
ተመልከት ስፈትል ዕየው ክናዴን ።
ፈጥኖ ይዘረጋል ይታጠፋል ቶሎ
ዘኃውን ሲፈትል ሲስብ አመልማሎ ።
አቀርብልሃለሁ ብዙ ዐይነት ስፌት
ሞሰብ ከቀለምሸሽ ወራንታ ሌማት ።
ቁልቢጥና ድርጎ ዕንቅብ ወራንታው
በጥቢ በጸደይ እኔ ምስፋው
ቍጥርም የለውና ማጀት ይቻለው ።

ል ብ ጥበብሽን ሙያሽን ስላየሁ እማዬ
ልቤ ተደሰተ ኰራ ሕሊናዬ ።
እረ ምን በልተሽ ነው እንደዚህ ያማረ፤
ክናድሽን ዐይቶ ልቤ ተቸገረ ።

ኢትዮጵያ ምበላውንማ ስንቱን ልቍጠረው
ሲሳይ ዘይንተረፍ እህሉ ብዙ ነው ።
ወሃ በሬ ብዬ ባርሰው ሜዳውን
ያብቅላል መሬቴ የምዘራውን ።

ወደ ዱር ብገባ ተራራ ብወጣ
ቍጥር የለሽ ፍሬ ዝቄ ነው ምመጣ ።
እንካሴዬን ይዤ ሐረግ ብቈፍር
ከማር የሚጣፍጥ አገኛለሁ ሥር ።
ወዲያ ወዲህም ብል በየጕራንጕሩ
መዛቅ መሸከሙ አሰለቸኝ ማሩ ።
ማሩ ሲሰለቸኝ ወደ ከብት ብሄድ
ሊወስደኝ ነበረ የወተት ሞገድ ።
በዝርዝር ባወጋህ ትሰለቻለህ
ሁሉም ሞልቷል እንጂ ምኑን ልንገርህ ፤
ስለዚህ አውርቼ ላልጨርስልህ ።
ሚበቅለውን ሁሉ በመላ አዝመራዬ
እህልና አትክልቱን በቈላ ደጋዬ ።

ል ብ ሁሉንም ነገረኝ እመ በጽሙና
ማሩ ንግግርሽ አይሰለችምና ።

ኢትዮጵያ እንተን ካልደከመህ ከሰማህ ሁሉን
አወራሃለሁኝ ቡና እየጠጣን ።
በቈለም በጉድሩ በጉና ፍየሉ
በጣም ያስጐመጃል ላስተዋለው ሁሉ ።
አርጆ ብቅ ብትል ብትወጣ ወለጋ
ታያለህ ተሰጥቶ የበጎቹን መንጋ ።
ቄለም ደምቢ ደሎ ገምቢ ጋር በሊሙ
ማለፊያም አይሰጥህ የነቀምቴ ላሙ ።
መንገድ አይገኝም ሜዳውን ሲዘጋ
በሺ የሚቈጥረው የነቀምቴ መንጋ ።
ገምቢ ጋር ተራራ በአንገር በቈላው
በጣሙን ያስፈራል ድምፁ የበሬው
ሲያገሳ እንዳንበሳ ተሩቅ ብትሰማው ።
ዛፍ ለዛፍ እያለች ጥሩዋ ጥገት
ሣሩን ቅጠሉን ውላ ስትቧግት
ማታ ትሰጣለች አንድ ቶፋ ወተት ።
ባርጆና በጉድሩ ላሜ ተዋለች
አንድ እንሥራ ወተት ትታለባለች ።
እሱሜና ቤጊ የሚታረደው
ስብ ሥጋ ብቻ ነው ብርንዶም የለው ።

ከላም ከበሬዬ ከበግ ከፍየል
የዱር እንስሳቱ እጅግ ይበልጣል ።
ባየሀ በቀመስኸው ሌላም አያስበላ
ቡኸርና ሰሳ ሚዳቋ ድኩላ
ወደደላው ጐሼ ቀጭኔና ሳላ ።
በወጥመዴ ይገሬ አድኜ ገድዬ
እኰመኰማለሁ ቋንጣውን ዘልዝዬ ።
በወፎችም በኩል ጅግራና ቆቅ አሉ
እንደ ደሮ ሁላ ጣፍጠው የሚበሉ ።
ርግቡ ቢተርፍ ዋኔና ቡላል
ሌላው ሲሳይ ሞልቶ ማን ይነካዋል ።
ሁሉን አወራሁህ በሥጋ በኩል
ማወጋህን ስማ ደግሞም ስለእህል ።
ባርጆና በጉድሩ በደጋ ደጋው
ጠመጅና ስንዴ አተር ባቄላው
እምቡጡ ቅልጥሙ ከባዱ ዛላው
በጣሙን ይገርማል ሂደህ ብታየው ።
በሊሙ በቄለም በቤጊ ባሱሣ
በግንቢ ነቀምቴ ሚበቅለው ዳጉሳ
እንዳለ ይቀመጥ ተወው አይነሣ ።
ሲጐናዘል ባየሀ ጤፉን ስዘራው
በማረው መሬቴ በወይና ደጋው ።
የምዘራው ባርጆ በቤጊ ጥጋት
የጤፌ ንጣቱ ይመስላል ወተት ።
አጃውን ስንዴውን በግንቢ ፈጭቼ
ቅቤውን አንጥሬ በቅመም መትቼ ።
ቤዴ ሚባለውን የጋላ ምጣድ
ማለዳ እጥድና ሰዓቱ ሳይረፍድ ።
ጭንቦዬን ጋግሬ ነባበሮ አንጕቼ
እውጠዋለሁኝ በቅቤ ፈትፍቼ ።
ጭንቦውን ቢበላ መቼም ሳያባራ
ይህ ልጇ ደበረ መሰለ ወጋግራ ።

ልብ እባክሽ እማዬ ከምታወሪኝ
በጣሙን ጐመጀሁ ትንሽ አቅምሺኝ ።

ኢትዮጵያ ሂድልኝ ከፊቴ ሳይዝህ ቀጠና

የደረስህበትን ቡናህን ጠጣና ።
ጭምቦ ሲሰለቸኝ በግንቢ ቄለም
እውጣለሁ ገንፎ ሚቸግር የለም ።
እህሉ ስለበዛ በቄለም ባገሬ
ከጠላው በቀረ የዳጉሳ አንጋሬ
ሰው ስለማይበላው ቂጣውን ጋግሬ
በጨው አጣፍጬ ይበላዋል በሬ ።
ከሰንዴ ከጤፌ ከጠመጇ ሌላ
አለልኝ በቆሎ ሼቱ የሚበላ
እንጀራው ያማረ ተስማሚ ለጠላ
ያበቅላል መሬቴ ብዙ ዓይነት ማሽላ ።
እውጠዋለሁኝ በጣም አሳምሬ
በወተት እያማግሁ በቅቤ ነክሬ ።
ጋግሬ አንጉቼ የዱሩን እንስት
ሳምገው ባየኸኝ በጊደር ወተት ።
ወደ ደጅ እንውጣ ላሳይህ ጐደሬ
የሸፈተ ፋኖ ይመስላቀ ጐፈሬ ።
ሙዝዬና ዕንጨቴ ቆሜ ኋደኛው
ቀቅዬ ብበላው ራቤን ከላው ።
ዕየው ያፈክራል ወፍ አራሹ ቡሬ
ክፉ ራብን ገዳይ ችጋር አባራሬ ።
ከቤቴ እወጣና በደጋ በቄላ
እንኮይና እንጆርይ እሼንም ስበላ
ይጠፋል ራቤ እንኳን ዋርካ ሾላ ።
ቅጠላ ቅጠሉን ሂጇ ደምቢዶሎ
ዶቅማና ዋንዛውን ለቅሜ ከበሎ
ስወጠውጥ ከዋልሁ ሆዴ መቼ ጐሎ ።
በበሎ በረሃ በዴዴሳ ወንዝ
የሚገኘው ፍሬ የሚያስንቀው ሙዝ
ሁሉም ተስማሚ ነው ሰውም አይመርዝ ።
በቄለም በረሃ ከበላ ቡቱጅ
መጠጥም አይሻ የመንደሬ ልጅ ።
ያስቃል ሲዘሉ በመላ ሰክረው
የቡቱጁን ፍሬ ልጆቱ በልተው ።
በጣም የሚጣፍጥ ከዱር ፍሬ ሁላ

አለልኝ አንድ ዛፍ ፍሬው የሚበላ
ጥሬው ይጣፍጣል ይጥማል ሲቈላ ።
በደንብ ለማስረዳት ቀጠሮ ስጠኝ
አሁን እንዳልነግርህ ስሙ ተረሣኝ ።
ጃ አለኝ ፍራፍሬ የዱሩ ሲሳይ
አጋምና ቀጋ እንኮይ ዶቅማ ሳይ ።
ዕፀዋትን ትቼ ልንገርህ ቅመም
እህልን አጣፍጦ ሚሰጠውን ጣዕም ።
ወፍ አራሽ ኽንጅብል ጥሩ ኮረሪማ
በቈለም በግምቢ በሊሙ ከተማ
ለልሳን ያማረ ለሆድ የተስማማ ።
አምጥቶ ይሸጣል ጕረምሳው ከዱር
ገቦ ሞልቶልኛል ምንም አይቸግር
በዱሬ ይበቅላል ሌላውም ቅመም
ዐወቆ ካልበቀለ ሚዘራው የለም
የቁንዶ በርበሬ ደግሞም ሚጥሚጣው
ይበቅላል በደኑ በዱር በጫካው

ል ብ — ክንድሽ የወፈረ ያወለወለው
ሳያስብ ቢበላ ባይቸግረው ነው ።
ነግረሽኝ ነበረ የዱሩን ሲሳይ
ረጃጅም ዕንጨት ዛፍም አለሽ ወይ ።

ኢ ትዮ ጵ ያ — ዛፉን እያየኸው በግቤ በሻምቦ
ከከተማው ሳትርቅ በኮምቶና የምቦ ።
በዴዴሳ ባንገር ደኑ እያለልህ
እንደምን ጠየቅኸኝ ዛፍ አለሽ ብለህ
በቀደም እንዳልሁህ የቅርቅኃው ዕቃ
በጣም ያኰራኛል በሊሙ በጡቃ
ረጅም ቅርቅኃ ያበቅላል ወለል
አንገርና አሱሣ ወፈፍራም ሽመል ።
ባሱሣ በቈለም በባሎ በረሃ
ሽመሉ ይመስላል የደጋ ቅርቃኃ ።
ትዝ ሲለኝ በረሃው ጫካውና ደኔ
አለቃቅሳለሁ ቊጭ ብዬ በውኔ ።
አረ ! ደኑ ደኑ ጫካው በረሃዬ
የአራዊት መፈንጫ የእንስሳት ሸኃዬ ።

ጥራኝ ዱሩ ጥራኝ ጕራንጕሩ
ላንተም ይሻልሃል ብቻ ከማደሩ ።
እንዲህ ሳንጐራጕር ያልፍልኛል ቀኑ
ጫካው ትዝ ሲለኝ ሲናፍቀኝ ደኑ ።
ና በል ተከተለኝ ላሳይህ ሁሉን
በየዱሩ ዙሬ ዛፍና ግንዴን
በአንገር በዴዴሳ በግምቢ በበሎ
በሊሙ ነቀምቴ ቄለም ደምቢዶሎ
እንኳንስ ዋርካና ትልቅ ዱር አባሎ
ዐይን ያነሆልላል ላየው አስተውሎ ።
ወፈፍራሙ ሰምበ ታላቁ ቀረሮ
አትቅረቡኝ ይላል በሩቅ ተገትሮ
ጨበና ውልክፋ ለንቋጣና ዋንዛ
ገተምና ዋርካ አይምሰልህ ዋዛ
እሼ ጥቀኑር ዕንጨት ይላሆና ሲላ
ይተከከላሉ ከመንደርህ ሾላ
ልታየው ብትፈልግ ከሥር ቁጭ ብለህ
የዛፉ ቅርንጫፍ ጫፉ ሲርቅህ
ከርዝመቱ ብዛት ያለቅሳል ዐይንህ
የሚያስገርም ዕንጨት ፍጥረቱ ለብቻ
ቅርፍቱ ተሰፍቶ የሚሆን ስልቻ
አሳይሃለሁኝ ትንሽ ቈየኝ ብቻ
በዴዴሳ ቈላ በሳገር በወለል
በጣም ረጃጅም ዕንጨት ይበቅላል ።
በዚሁ በዱሬ በየበረሃው
የሚተመው ንቤ መስፈርትም የለው
ዕጩ ትዝ ሲለኝ ሲናፍቀኝ ማሩ
አማጋ እቈርጣለሁ ብየጉራንጕሩ ።
ከዛፉ ላይ ወጥቶ ቀፎ ሲሰቅል
ንብ አናቢው ልጄ ትንኝ ይመስላል ።
ዛፉ ስላማረ ባርጆና በጉድሩ
ባየኸኝ ስቈርጠው ለብቻው ነው ማሩ
ባየኸኝ ስቈርጠው ለብቻው ነው ማሩ ።
የተንኝ ማር አለኝ የሚያጠፋ ሳል
ከጕራንጕሮና ከሆማ ገደል

አረባና ንቤን በሰፊው ገንዳዬ
እመላለሁ ማሬን እንደ ልቡናዬ
ማሬን ሰብስቤ አንዳችም ሳይተርፍ
ቀፎዬን ሰቅዬ ከረጅሙ ዛፍ ።
እመለሳለሁኝ ወደ ቤት በጤና
ማሬን ተሸክሜ በታላቅ ቅምጫና
በበሬ አቅማዳ በፍየል ስልቻ
ታያለህ ስመጣ ትንሽ ቈየኝ ብቻ ።
ዱር ለዱር የሚገኝ ብዙ ጣዝማ አለኝ
ለጤናም ይበጃል ማርም አያምረኝ ።
ንቧን አራግፌ ማሬን ከቈረጥሁ
ቀፎዬን ሰቅዬ እመለሳለሁ ።
ማርም ከፈለግሁኝ እንደ ልቡናዬ
ለንቤ እሠራለሁ ገንዳ ከንሮዬ ።
ጣዝማ የምትቃዋው ንብ የምትቀሥመው
አልባብ አልባብ ይላል የዱሬ አበባው ።
በኮምቶ በረምቦ በግንቢ ቈለም
የሚበቅለው ዛፌ ወደር የለውም ።
በዴዴሳ ባንገር በበሎ መረሃ
መላ ነው ሸንበቆ ለምጥም ችብኃ
በወለል ተራራ ረጅም ቅርቃኃ ።
ይመስላል ደብተራ የተማረውን
ሲዘምም ብታየው ነፋስ ዝማሜን።
የላስቲኩ ሐረግ በጣም ዝነኛው
ያገሬ ተራራ ደኑና ጫካው
ምንም አያሳልፍ እሱ ብቻ ነው ።
ል ብ    እኔም ስቅለበለብ ከጫካሽ ገብቼ
ቀልጬ ነበረ መንገዱን አጥቼ ።
ሐረጉ ሲለቀኝ ግንዱ ሲያግደኝ
መለጉ ተብትቦ ዳዋው ሲጥለኝ
ቀልጬ ነበረ ያ መሀሊህ ውጦኝ ።
ባንገር በዴዴሳ ያለው መላሽማ
በቈለም በበሎ የበቀለው ውድማ
ፈሪ እንዳይደነግጥ እንዲያው አይስማ ።
ቃትቼ ቃትቼ ድካሜ ሲበዛ

ተቀምጬ አይ ጀመር ዝንጅሮ ጉሬዛ
ኽም ኽም እያለ መህሎሽን ሲገዛ፤
በሚገዛው ሀገር ሂጄ ያለ ይለፍ
ታሥሬ ነበረ ልጅሽ ስክለፈለፍ ።
አቶ መታከተን ጠራሁና ዋስ
ተፈጥሜ መጣሁ ደግሜ ላልደርስ ።
ተነጥፎ ዐየሁትኝ ከታላቁ ግንድ
የዥንጀሮው ዙፋን የዝንጀሮው ዘውድ
ጳጳሱ ጉሬዛ ጽሕሙ ምን ያምር
ጉብ ብሎ ለሚያየው በዛፉ ወምበር
በንጉሡ አጠገብ በታላቅ ክብር
አገፋሪ ጦጣ ሕዝቡን ሲያጋፍር
ከዚያ መሀል ገብቶ ማነው ሚናገር ።

**ኢትዮጵያ** ደኑን እያወቅሽው ራስህ አይተህ
ዱር አለሽ ወይ ብለህ ምነው የጠየቅህ

**ልብ** በዴዴሳ በሎ በሊሙ በንገር
ይለፍ ስለሌለኝ ባንበሳው አገር ።
ያሱሳን በረሃ የቄለምን ደን
አጥርቼ በላውቀው ቄላ ቄለውን
አስፋፍተሽ ልትነግሪኝ ጠየቅሁሽ ሁሉን ።
ዘመቻው ካልቀረ ወደ በረሃው
ቄላ ከወረድን ዱሩን ካየነው ።
እማዬ ንገሪኝ ያራዊቱን ዝና
አስፋፍቶ መናገር ባንቺ ያምራልና

**ኢትዮጵያ** ነግሬሃለሁኝ የዱሩን እንስሳ
ትንሹን ትልቁን ሁሉም ባይወሳ
ሚበላውን ሁሉ መድገም አያሻም
ተነጋግረነዋል ከዚህ በቀደም ።
አሁን የማወጋህ የዱር አራዊት
በጣም የሚያስገርም ታላላቅ ፍጥረት ።
በበሎ በረሃ አንበሳው ቢያገሳ
ሀገር ተጨነቀ ተሸበረ እንስሳ ።
ቡኸር ፈረጠጠ ድኩላው ተነሣ
ዘለው ውድማ ገቡ ወንድምቢ ደፋርሳ ።
አራዊት ታወከ ባንገር ባዴዴሳ

ተሸበረ ከብቱ በግምቢ ባሱሳ ።
በጉድሩ በሊሙ ባርጆ በደጋው
ተሸበረ ላሙ መድረሻው ጠፋው
ዝሆን ሲግበሰበስ በየበረሃው
ተራራ ይመስላል በሩቅ ለሚያየው
የሚዳው አህያ አውራሪስ ግስላ
በየዱሩ ብታይ አነርና ተኩላ ።
ይመስላል በሩቁ የዘላን በረት
ቊጥር የለሽ መንጋ የታጐረበት ።
ኮርቄውን ለመያዝ ይሳባል ነብር
ሲጨነቅ አንበሳ ቡኸርን ሊሰብር ።
ሰለደን ስላአወሬ እንግዲህ ይብቃህ
ወንዞቹ ትዝ አሉኝ ትንሽ ልንገርህ ።
በአርጆና በጉድሩ በደጋ ደጋው
በቀሌም በወለል በጋራ ጋራው
ይፈልቃል ብዙ ምንጭ ቊጥር የሌለው ።
ዱር ለዱር ሲሄድ የጠራው ውኃዬ
ቀድቼ ብጠጣ እንደ ልቡናዬ
ፊቴ አብረቀረቀ ወፈረ ገላዬ ።
የገባን የበርበር የታላቁ ባሮ
ስፋቱ ጥልቀቱ አያልቅም ተነግሮ ።
የታላላቁ ወንዝ ያንገር የዴዴሳ
ያሣቸው ብዛቱ ይቅር አይነሣ
ከዳር ሲገላበጥ ልቡና ሲያሳሳ
የሚያዝ ይመስላል እንደ ሞኝ እንስሳ ።
ቄርጬ ከትክቼ የደኔን ዕንጨት
ላክሁት በዴዴሳ ጫጭኜ ትላንት ።
ታላቁን ቀረሮ አሁን እፈልጣለሁ
አሥሬ ጠፍሬ ነገ እልከዋለሁ ።
የበረሃው መርከብ ዴዴሳ ሳለልኝ
ሰምቦ ኮማን መላክ ምንም አይቸግረኝ ።
ና እንሂድ ላሳይህ እንውጣ ወለል
በተራራው ዙሪያ ከደጋው መሃል
የሚፈልቀው ምንጬ መቶ ይሆናል ።
አዙሬ አሳየሁህ ወንዝ ተራራውን

አቀበት ቍልቍለት ሣር ቅጠሉን
ቈላ በረሃውን ወይና ደጋውን ።
እንድለብስ ጨጓራ እንዲለማ ሀብቴ
የሚወልበትን የዘላኑ ከብቴ ።
ላምና በሬዬ ይመስላል ጐተራ
ሣር እያበላሁት ካጠጣሁት ሆራ ።
መንጋዬን ስጠብቅ ሌቱን ተጕልቼ
ሰብሌን ስሰበስብ ሌት ተቀን ተግቼ ።
የሌት ሕመም ደዌ ብርድ እንዳይበርደኝ
በሽታ ቅርጭጭት ቈምጦ እንዳይጥለኝ
የድፎ መታጠብያ ፍል ውኃ ጣድሁኝ ።
ይኸውም ፍል ውኃ ነውና መዋት
ለሄደበት ሁሉ ይሰጣል ሕይወት ።
በጨረም ቀጥቅጦ ቈሌም ሐረጉባ
የታጠበ ሁሉ እየዳነ ገባ ።
በበሎ በረሃ የቈላው ቍስል
ሐረጉባ ሲደርስ ምሎ ይለቃል ።
የመዋቴን ሥራ ስንቱን ልንገርህ
ራስህ ተረዳው ሲፈውስ ዐይተህ ።
ብዙ መዋት አለኝ በየበረሃው
በደንብ ያልተበጀ እኔ ማላውቀው
ድውይ የሚፈውስ ቍጥር የሌለው ።

ል ብ — ወንዝና ተራራ ዱር ትወጃለሽ
ምንም ብታወሪ አያልቅም ወሬሽ
እባክሽ አድምጪኝ ወግሽን አቋርጠሽ ።
የዴዴሳ ማዕበል ያንገር ፍላሎት
የግቤ ፏፏቴ የገባን ሙላት
በጣም የታወቀው የባሮ ጅረት
ያሻግርሻል ወይ ያላንዳች ፍርሃት
ሞልቶ ሲጥመለመል በለቆ ክረምት

ኢትዮጵያ — ዴዴሳ ቢሞላ ምንም አልፈራው
አለኝ ጥሩ ድልድይ ልጄ የሠራው
ደጃች ገብረ እግዚአብሔር ጥበበኛ ሰው
ሠርቶልኝ አለፈ ነፍሱን ይማረው ።
አዲስ ድልድይ አለኝ ለገባን ለጊቤ

አኳኋኑ ሁሉ በጣም ደነቀኝ
መቼ እንደሠራሽው እስቲ ንገሪኝ ።

<u>ኢትዮጵያ</u> በሃያ አንድና በሃያ ሁለት
እንዴት ያምር ነበር ከጣሊያን በፊት ።
መመላለሻ አጥቶ ዓለም ሲቸገር
መድኃኒት አምጥቼ ከባሕር አገር
ብዙ ሕመምተኞች እፈውስ ነበር ።

<u>ል ብ</u> አሁንስ ተስፋፍተዋል በብዙ ዘመን
ማን መሠረተልሽ መጀመሪያውን ።

<u>ኢትዮጵያ</u> ልነግርህ ከፈለግህ ነገሩን ከሥሩ
ወደዚህ የገቡ ወንገል ሊያስተምሩ
ከስዊድን ሚሽን ታዘው ከማኅበሩ
ትምህርት ቤቱንና ሆስፒታሉን ሠሩ ።
ሐኪሞች ነበሩ በጣም የሚለፉ
ሕዝብ ያገለገሉ ሌት ተቀን ሳያርፉ ።
ሀገሬን ለመውረስ ጣሊያን መጣችና
ብታደፈርሰው ይህን ሁል ባልትና ።
ሆስፒታል ተዘግቶ አኪሙ ተሰዶ
ከታች ሁኜ ሳለቅስ ልቡናዬ ነዶ ።
በድል አድራጊነት ጠቅል ሲመለስ
ሐኪሞቼ መጡ አገኘሁኝ ፈውስ ።
ካለፈልኝ ወዲህ የጠላት ወረራ
ሕዝቤን አክማለሁ ከመንግሥቱ ጋራ ።
ነቀምቴ በሞላ ልቡ ደስ ተሰኘ
በተፈሪ ጥበብ ጤና ስላገኘ ።
በትምህርትም በኩል አለኝ ብዙ ርምጃ
በእያውራጃው ቁሚል አንደኛ ደረጃ ።
ብዙ ትምህርት ቤት ነቀምቴ ከተማ
ስሙ የታወቀ ዝናው የተሰማ ።
ሁሉም ያስተምራል ተባብሮ አንድነት
በመላ ወለጋ ሚስዮን መንግሥት ።
እንዲህ በትንሹ የተማሪ ቤቱ
ተነግሮ የማያልቅ ሰፊ ነው አርእስቱ ።
አወጋሁ አወራሁ አሁንስ ደከመኝ
ወሬ ወዳጅ ልጄ ተነሥተህ ሂድልኝ ።

ሙላትም አልፈራ ስሄድ እንደ ልቤ ።
በባሮና ባንገር ባባይ በትልቁ
እንሻገር ብለው መዋኘት ማያውቁ
ባዘና በሙላት ተጠልፈው አለቁ ።
ጥቅሙን እናውራ እንጂ ታላላቁ ወንዝ
ድልድይ ካልተሠራ ነው የሰው ልጅ መርዝ ።
ውኃ ዋና እንኳ ቢያውቅ ልጇ ኃውለኛው
ምን ሊያረግ ይችላል ሙላት ሲመታው
ሳያስበው ድርሶ አዘ ሲነጥቀው ።
በጐጃምም በኩል ዐባይ እስቲሻር
ቁጥር የለሽ ልጆቼን እቀብር ነበር
ድልድይ እሠራለሁ ለድረቱ ሁላ
ዘመዴን እንዳይወስድ ልጄን እንዳይበላ ።
በቅርብ ሊሠራ ነው ያስብሁትኝ አቅድ
ከነቀምቴ አሱሣ ረጅም መንገድ ።
ምንም አልለወጠ መሐንዲሱ አሁን
ደጃች ሀብተ ማርያም የቀየሰውን ።
ከግቤ ጀምሮ አሱሣ ድረስ
ጸደቀ በመላ የሠራው ቅይስ ።
ሌላው ይቅርና ርቀን ሳንሄድ
ነቀምቴ ከተማ የሠራው መንገድ
የቀየሰው ቅይስ የከተማው አቅድ ።
እስከ ዛሬ ድረስ አንዱ አልተለወጠ
አልመጣም መሐንዲስ ከሱ የበለጠ ።
ለጤና ጥበቃ እንዳለሽ እማዬ
ታሪኩን ንገሪኝ ልስማ በጆሮዬ

ኢትዮጵያ
እንኳን ና ማውጋት አሳይሃለሁ
አንተን ካልደከመህ ሁሉን እያዘርሁ ።
ያለሙ በሽታ ሰውን አሰቸጋሪ
አገር ጥሎ ጠፋ ምሎ በተፈሪ
ወደዚህ ሚመጡ ብዙ እመምተኞች
ድነው ይሄዳሉ በጥቂት ቀኖች ።

ልብ
የሐኪም ቤቱን ክፍል ዞሬ ዐየሁልሽ
ደግሞም መድኀቱን አስተዋልሁሽ
በቤቱ ንጽሕናም ተገረምሁልሽ ።

ል ብ

መወድስ ሰጥቼ ለሥራሽ እማዬ
ልሂድ ወደ ቤቴ ደኅና ዋይ ብዬ ።

## መ ወ ድ ስ ።

የወርቅ ማሠሪያሽ ታየኝ በአንክሮ ሕሊና
በእግረ ሕሊና ዐሳብ ከምኞት ሀገር ባዕድ
መጥቶ ሲጐበኘው ሁሉም በዚህ ዓለም ያለ ነገድ
ወርቅ አምባር አድርጓልና
እጅግ ባለሙሉ ደም ወለጋሽ ክናድ
ስለዚህም በጣም ኰሪ
ደም ግባት ያለሽ እጅግ ኢትዮጵያችን ወላድ።
ካደባባይሽ ትላንትና ሲናገር ሰማሁ ዘመድ
በክንዱ የያዘችው ወርቅ ያበቃል ብሎ ለዘውድ
በታየች ጊዜም ከሩቅ ታስጐመጃለች ወንድ
በወርቅ የጠለቀች ወለጋ ልጃገረድ ።